የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጥንታዊያን ገዳማት ዛሬ

፫ የርእዮተ ዓለም /Ideology/ ለውጦች

የኮሙዩኒስት ሥርዓት አንዱ አካል የሆነው የ"አምላክ የለም" ፍልስፍና ጸረ-ሃይማኖት አቋም ሕዝቡ ለሃይማኖቱና ለገዳማቱ የነበረውን ክብር አሳጥቶታል። ለገዳማት ይደረግ የነበረውን የችሮታ ሥራዎች /ድጋፎች/ ቀንሷል።

ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን



ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን




፬ ድርቅና ወረርሽኝ

በኢትዮጵያ በተከሰቱት ተደጋጋሚ ድርቅና የበሽታ ወረርሽኝ ምክንያት የሕዝቡ በተለይ የአርሶ አደሩ ኑሮ በመጎሳቆሉ ገዳማትን እንዳይደግፍ አድርጎታል። መነኰሳትና መምህራንም በረሃብ ተፈትነዋል፣ በወረርሽኝ አልቀዋል። በዚህም ምክንያት የመነኰሳት አንድነት ተፈትቷል፣ መምህራን ወንበር አጥፈው ተማሪዎቻቸው ተበትነዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ችግሩን በጽናት ተጋፍጠው ቅርስን የጠበቁ፣ በረሃብ እየሞቱ ቅርስን ያኖሩ መነኰሳት አሉ። ለምሳሌ ሳይኮ ኪዳነምሕረት፣ ፈለገ ጥበብ ቅድስት ቤተልሔም እና የትግራይ ገዳማት ናቸው።



ደብረ ምዕራፍ ቅ/ማርያም ቤ/ክ



ደብረ አባይ አቡነ ሳሙኤል ቤ/ክ



ቅድስት ቤተልሔም ቤ/ክ

ADWEST Tel: 011 515-0236